# IMPLEMENTATIONOF E-SCHOOL SOLUTION

**Sponsored By:** Innovation and Technology Development Bureau (ITDB)

## የተማሪዎች የኦንላይ ምዝገባ መመሪያ

## ለተማሪዎች የተዘጋጀ

በትሪያ ትርሬዲንግ
የተዘጋጀ
ሰኔ 2016 ዓ.ም

# 1. መግቢያ

**ይህ መመሪያ ስለ ምንድን ነው?**

ይህ መመሪያ የ E-School system በመጠቀም ተማሪዎች በ የትምህርት ቤቶቻቸው እንዴት መመዝገብ እንደሚችሉ መረጃ ይሰጣል።

**የE-School ሲስተም ጥቅም**

አሁን ያለውን የሥልጠና እና የትምህርት ሥርዓት ለማቀላጠፍ የ E-School system ተዘጋጅቷል። ይህ ሲስተም አመልካቾች እንዲያመለክቱ፣ የትምህርት ሂደታቸውን እንዲከታተሉ እና የምዝገባ ሁኔታ ዝርዝሮችን እንዲቀበሉ ያስችላቸዋል።

**ለስኬታማ ምዝገባ ምን ማዘጋጀት አለብኝ?**

የE-School system በአግባቡ ለመጠቀም ፤ እባክዎ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟሉ።

1. ኮምፒውተር (ዴስክቶፕ ወይም ላፕቶፕ ሊሆን ይችላል) ወይም ስማርትፎን
2. የበይነመረብ ግንኙነት/ኢንተርኔት (የተሻለ የ ኢንተርኔት ግንኙነት ያለበት ስፋራ ላይ እንዲጠቀሙ ይበረታታል)
3. የድር አሳሽ "ብራውዘር" (ክሮም፣ ማይክሮሶፍት ኤድጅ፣ ሞዚላ ፋየርፎክስ እና የመሳሰሉት)
4. የተማሪውን ማንነት በሚገባ የሚያሳይ የተማሪ ፎቶ ግራፍ
5. የልደት ሰርተፍኬት (ተማሪው ካለው)
6. የተማሪው የባለፈው ሪፖርት ካርድ

   ለምሳሌለ 5 ኛ ክፍል የሚመዘገብ ተማሪ የ 4 ኛ ክፍል ካርድ)

7. የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፎቶ ግራፍ
8. የወላጅ ወይም የአሳዳጊ መታወቂያ


## 2. በE-School ሲስተን እንዴት መመዝገብ እችላለሁ?

1. የክሮም፣ ማይክሮሶፍት ኤድጅ፣ ሞዚላ ፋየርፎክስ እና የመሳሰሉትን ድር አሳሽ "ብራውዘር" ይክፈቱ እና


2. ለትምህርት ቤትዎ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የቀረበውን ማገናኛ/URL አስገቡ በመቀጠል የ"Enter" ቁልፍን ይጫኑ።

   የ ትምህርት ቤትዎ አድራሻ የሚከተለውን ቅርጽ የሚይዝ ይሆናል።


   ***ለምሳሌ:*** https://myschoolname.addislearning.edu.et




3. በትምህርት ቤቱ ፖርታል መነሻ ገጽ ላይ የ"Online Admission" አማራጭን በመፈለግ ለመመዝገብ ይጫኑ።



ደረጃ 3፡ በተማሪው መሞላት ያለባቸውን መረጃዎች የያዘ የምዝገባ ቅጽ በዚህ ገጽ ላይ ይታያል።




የተማሪ ምዝገባ ገጽ ከተከፈተ በሁዋላ፡-

- ✧ Education Program የሚለውን የአማራጭ ሜኑ በመጠቀም የመደበኛ፣ የማታ፣ የርቀት ትምህርት፣ የአዋቂዎች መሰረታዊ ትምህርት (ABE) እና ተግባራዊ የጎልማሶች ትምህርት (FAL) ከሚሉት ምርጫዎች መካከል እርሶ የሚመዘገቡበትን የ ትምህርት ፕሮግራም ይምረጡ።
- ✧ "Applying Grade" የሚለውን የአማራጭ ሜኑ በመጠቀም ተማሪው የሚያመለክትበትን ክፍል ይምረጡ።




እንደ የተማሪ ስም ፣ የትውልድ ቀን ፣ የመኖሪያ አድራሻ ፣ ስልክ ቁጥር ፣ ኢሜል እና የመሳሰሉትን መረጃዎች በሙሉ በትክክል ይሙሉ ፣ በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ ትክክለኛውን ፋይል ያስገቡ።

- ✧ Personal Data የግል መረጃ ክፍል፡-

o የተማሪውን ሙሉ ስም (የተማሪውን ስም ፣ የአባት ስም እና የአያት ስም) ፣ ጾታ ፣ የትውልድ ቀን (DOB) ያስገቡ እና ከሚዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ የተማሪውን ዜግነት ይምረጡ።


o የተማሪውን እናት ሙሉ ስም ( ስም, የአባት ስም እና የአያት ስም) ያስገቡ።

o ተማሪው የመደበኛ ትምህርት የጀመረበትን አመት ያስገቡ።(1)

o "Language used for learning" አማራጭ ሜኑ በመጠቀም ለተመረጠው ክፍል (English, Amharic and Afan Oromo) ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ይምረጡ። (2)

o የተማሪውን የልደት የምስክር ወረቀት ለ ቅድመ-አንደኛ ተማሪዎች ብቻ (3)፣ የ ተማሪውን የቅርብ ጊዜ የሪፖርት ካርድ (4) እና የተማሪውን ፎቶ (5) ያስገቡ።

o አንድ ተማሪ ልዩ ፍላጎት እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ "Special Need " ክፍል ውስጥ "አዎ" የሚለውን አማራጭ ይምረጡ እና ከ አማራጭ ሜኑ ውስጥ ተዛማጅ የሆነውን ልዩ ፍላጎት ይምረጡ። ብዙ አማራጮችን መምረጥ እና በዝርዝሩ ውስጥ የሌለ ሌላ አማራጭ ማከል ይችላሉ.





✧ Place of Birth/ የትውልድ ቦታ ክፍል:

o ተማሪው/ዋ “Ethiopian” የትውልድ ቦታ አድርጎ ከመረጠ/ጠች ከተማ/ክልል፣ ክፍለ ከተማ/ዞን እና ወረዳ መስኮች መረጃ በመስጠት የተማሪውን የልደት ዝርዝር ሁኔታ ያስገቡ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ከተወለደ የተወለደበትን ሃገር ያስገቡ ።

o ተማሪው/ዋ ከሌላ ትምህርት ቤት የተዘዋወረ ከሆነ በ“transfer student” ክፍል ውስጥ “አዎ” የሚለውን አማራጭ ይምረጡ እና የበፊት የትምህርት ቤት ስም (7) ፣ የድሮውን የተማሪ መታወቂያ (8) እና ከቀድሞው ትምህርት ቤት መልቀቂያ ደብዳቤ ያስገቡ(9)።


o ከተማ/ክልል፣ ክፍለ ከተማ/ዞን፣ ወረዳ፣ የቤት ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር እና ኢሜል በመሙላት የተማሪውን ወቅታዊ የመኖሪያ አድራሻ ይግለጹ።




✧ የወላጅ/አሳዳጊ መረጃ፡-


o ሁሉንም አስፈላጊ የወላጅ/አሳዳጊ ዝርዝሮችን ይሙሉ።

o የወላጅ/የአሳዳጊ መታወቂያ (10) እና የወላጅ ፎቶ (11) ያስገቡ።





✧ የወላጅ አድራሻ አስገባ። የወላጅ አድራሻ ከተማሪው አድራሻ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣ “Click if the same as student address” የሚለውን አመልካች ሳጥን ይምረጡ።

✧ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ካስገቡ በኋላ ከማመልከትዎ በፊት ዝርዝሩን አንድ ጊዜ ለማየት **“Preview”** የሚለውን ቁልፍን ይጫኑ።





በ **“Preview”** ገጹ ላይ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ይውረዱ እና እያንዳንዱ የተማሪው መረጃ በትክክል መመዝገቡን ያረጋግጡ።

የሚለወጥ መረጃ ካለ **“Edit”** ን ይጫኑ እና ወደ “Online Admission” ገጽ ይመለሱ።





ዝርዝሮቹ በትክክል ከተመዘገቡ **"Confirm"** የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።




✧ ሌላው አማራጭ በቀጥታ **"Apply"** የሚለውን ቁልፍ መጫን ይችላሉ.





ደረጃ 4፡ በተሳካ ሁኔታ ሲጠናቀቅ፣ ጊዜያዊ የምዝገባ መታወቂያ፣ ስልክ ቁጥር እና ያመለከቱበትን ቀን የያዘ የማረጋገጫ መልእክት ይታያል። የማረጋገጫ መልእክቱ **"Print"** እና **“Download”** የሚለውን ቁልፍ በመንካት ሊታተም እና ሊወርድ ይችላል።







በተጨማሪ ኢሜል ወይም ስልክ ቁጥር ያስገባ ተማሪ የማመልከቻውን ማረጋገጫ በኢሜል ወይም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት /SMS ይቀበላል።




# 3. የምዝገባ ሂደቴን እንዴት መከታተል እችላለሁ?

የተማሪው/ዋ የምዝገባ ፎርምን በትምህርት ቤቱ አስተዳደር አማካኝነት ካልፀደቀ/ተቀባይነት እስካላገኘ ( Approve እስካልተደረገ) ድረስ የተማሪው/ዋ ምዝገባ ሂደት አልተጠናቀቀም:: ስለሆነም ተማሪው የምዝገባ ሁኔታን ለመከታተል በትምህርት ቤቱ ዌብሳይት በመነሻ ገጹ ላይ ያለውን የ"**Status**" አማራጭ በመጠቀም የምዝገባ ሁኔታውን/ዋን ማረጋገጥ ይችላሉ።ይህንን ለማድግ የሚከተሉት ሂደቶች ይጠቀሙ

- የትምህርት ቤትዎን "website" በድር አሳሽ "ብራውዘር" ይክፈቱ።
- በመነሻ ገጹ ራስጌ ላይ የሚገኘውን የ"Status" ምርጫን ይጫኑ።





- በማረጋገጫ መልእክት ውስጥ የደረስዎትን የምዝገባ መታወቂያ  እና ስልክ ቁጥር ያስገቡ እና **"Get Result"** የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።





- የተማሪው/ዋን የምዝገባ ሁኔታ በምዝገባ ሁኔታ ሳጥን ውስጥ ማየት ይችላሉ። የምዝገባ ሁኔታውን "Print" የሚለውን ቁልፍ በመጫን ማተም ይቻላል።




የተማሪው የምዝገባ ሁኔታ ከሚከተሉት የአንዱን ያገኛሉ፡

1. **Pending:** በመጠባበቅ ላይ የምዝገባ ፎርም
2. **Approved:** የፀደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ

3. **Rejected**: ውድቅ የተደረገ የማመልከቻ ፎርም

4. **Resubmitting**: በድጋሚ ማመልከት

በሚል ይገለጻል። ተማሪው/ዋ የአስተያየት ክፍልን በመመልከት ስለ ማመልከቻቸው በትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተሰጠውን አስተያየት ማየት ይችላሉ።

**በመጠባበቅ ላይ/Pending ፡-** የማመልከቻው ሁኔታ በመጠባበቅ ላይ ያለ ከሆነ፣ በትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር እስካሁን አልጸደቀም/አልተቀበለውም/ዳግም ማስገባት አልጠየቀም ማለት ነው። ተማሪው/ዋ የተወሰነ ጊዜ መጠበቅ እና የማመልከቻውን ሁኔታ እንደገና ማየት አለበት/ባት።


**ተቀባይነት ያለው/Approved ፡-** የማመልከቻው ሁኔታ ተቀባይነት ያለው ከሆነ ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር ለትምህርት ዘመኑ ተመዝግበዋል።

**ውድቅ የተደረገ/Rejected፡-** ማመልከቻው "ተቀባይነት የለውም" የሚል ምልክት ተደርጎበታል ማለት፤ የተማሪው/ዋ ማመልከቻ ልክ አይደለም ፤ ትምህርት ቤቱ ተማሪውን/ዋን ለትምህርት አመቱ መቀበል አይችልም።

**በድጋሚ ማመልከት/ Resubmitting**: **፡-** ማመልከቻው እንደገና እንዲገባ ከተጠየቀ አንዳንድ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው መረጃዎች አሉ። ተማሪው/ዋ የ"Re-Apply" ቁልፍን በመጫን እና የማመልከቻ ቅጹን በመሙላት እንደገና ማመልከት ይችላሉ።

***ማስታወሻ***

ተማሪው/ዋ ስለ ማመልከቻው ሁኔታ የኢሜል ማሳወቂያ እና የኤስኤምኤስ መልዕክት ይደርሳቸዋል።



Your application is rejected Inbox

info@aatvetb.edu.et

to me, cc

12:26 PM (4 minutes ago)

**Dear ThomasMengstuMuluken,**


This is to inform you that your admission for Jerusalem Primary School has been rejected.

We appreciate your interest in Jerusalem Primary School, and we wish you all the best in your future endeavors.

**Sincerely,**

**Jerusalem Primary School**

የተማሪው/ዋ ማመልከቻው በትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር ተቀባይነት ካገኘ ፤ ተማሪው/ዋ የተመዘገበበትን የትምህርት ቤት ዌብሳይት አድራ/URL ፣ የተጠቃሚ ስም እና የይለፍ ቃል የያዘ የኢሜል ማሳወቂያ እና የኤስኤምኤስ መልዕክት ይደርስዎታል። ተማሪው/ዋ የተጠቃሚውን/ዋን ስም እና የይለፍ ቃል በመጠቀም ወደ ትምህርት ቤቱ ሲስተም ላጥ መግባት ይችላሉ።



**Hi,**

Your registration process is completed successfully on Addis Ababa Education Bureau (AAEB) E- School platform.

Url: **https://jerusalem.sims.uat.ethiocheno.com/**

UserName: **betelhemkokeb@gmail.com**

Password: **eschool@123**


## 4. በድጋሚ ማመልከት-Resubmitting

በት/ቤቱ ለመመዝገብ ያመለከተ/ተች ተማሪ በመጀመሪያው ማመልከቻ ላይ ያሉትን ስህተቶች በማረም ወይም በትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር የተመለከተውን የጎደሉትን ሰነዶች/ዝርዝሮችን በማከል በድጋሚ እንዲያመለክቱ ሊጠየቁ ይችላል።


በድጋሚ ለማመልከት የሚከተሉትን ሂደቶች ይከተሉ:-

ደረጃ 1: የትምህርት ቤትዎን "website" በድር አሳሽ "ብራውዘር" ይክፈቱ።


ደረጃ 2: በመነሻ ገጹ ራስጌ ላይ የሚገኘውን የ"Status" ምርጫን ይጫኑ።




ደረጃ 3: በማረጋገጫ መልእክት ውስጥ የደረስዎትን የምዝገባ መታወቂያ  እና ስልክ ቁጥር ያስገቡ እና "Get Result" የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።





ደረጃ 4: የተማሪው/ዋን የምዝገባ ሁኔታ በመግቢያ ሁኔታ ሳጥን ውስጥ ያረጋግጡ። የምዝገባ ሁኔታው በድጋሚ ያመልክቱ የሚል ከሆነ ለበለጠ መረጃ የአስተያየቱን ክፍል ያንብቡ እና የ"Reapply" ቁልፍን ይጫኑ።





ደረጃ 5: የ"Reapply" ቁልፍን ከተጫኑ በኋላ ያስገቡትን የምዝገባ መረጃ ዝርዝሮችን በምዝገባ መሙያ ቅጽ ላይ ያገኛሉ፣ አስፈላጊውን እርማት እና ፋይሎችን ያስገቡ።




ደረጃ 6: አስፈላጊውን እርማት ካደረጉ በኋላ የ"Apply" ቁልፍን ይጫኑ።





ደረጃ 7: ማመልከቻው እንደገባ የማረጋገጫ መልእክት ይደርስዎታል። በትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር ማመልከቻው ተቀባይነት እስኪያገኝ ድረስ ተማሪው/ዋ የተወሰነ ጊዜ መጠበቅ እና የማመልከቻውን ሁኔታ እንደገና ማየት አለበት/ባት።





ደረጃ 8: ተማሪዎች የምዝገባ ቅጹን እና የማመልከቻ ሁኔታን ማውረድ ይችላሉ።


✧ የማመልከቻ ሁኔታን ለማውረድ ከ"Print" አማራጭ ቀጥሎ የሚገኘውን የ"Download" መለያ ይጫኑ።




ፋይሉ ወደ ኮምፒውተርዎ ይወርዳል። የማመልከቻውን  ሁኔታ መክፈት እና ማየት ይችላሉ።





✧ የማመልከቻ ቅጹን ለማውረድ ከ"Admission for preview" ስር የሚገኘውን የ"Download" መለያ ይጫኑ። ፋይሉ ወደ ኮምፒውተርዎ ይወርዳል።



ፋይሉ ወደ ኮምፒውተርዎ ይወርዳል። የማመልከቻ ቅጹን በመክፈት ያስገቡትን መረጃ ማየት ይችላሉ።





## 5. የረሳሁትን የምዝገባ መታወቂያ/Admission Id በድጋሚ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪው/ዋ የምዝገባ መታወቂያው/ዋን ዝርዝር ማውረድ ወይም ማተም ባይችሉ እና የምዝገባ መታወቂያው/ዋን ሊረሱ ይችላል። ስልክ ቁጥር እና የምዝገባ መታወቂያ የምዝገባ ሁኔታን ለመከታተል ስለሚያስፈልግ ፤ የሚከተሉትን ሂደቶች በመከተል የጠፋዉን የምዝገባ መታወቂያ በድጋሚ ማግኘት ይቻላል።


ደረጃ 1: የትምህርት ቤትዎን “website” በድር አሳሽ “ብራውዘር” ይክፈቱ።

ደረጃ 2: በመነሻ ገጹ ራስጌ ላይ የሚገኘውን የ”Status” ምርጫን ይጫኑ።


ደረጃ 3: በሁኔታ ገጹ ላይ  የ“forget admission Id” ቁልፍን ይጫኑ።




ደረጃ 4፡ በሚመዘገቡበት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለውን ኢሜል እና ስልክ ቁጥር ያስገቡ እና "Reset admission Id" የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።




ደረጃ 5፡ የአንድ ጊዜ ኮድ (OTP) በኢሜል ወይም በኤስኤምኤስ ይደርስዎታል። ኮዱን ያስገቡ እና "Verify"የሚለውን ቁልፍ ይንኩ።






✧ የአንድ ጊዜ ኮድ (OTP) ካስገቡ በኋላ የምዝገባ መታወቂያዎን (admission ID) በኤስኤምኤስ ወይም በኢሜል ይደርሰዎታል።




✧ “Admission ID” ወይም የመግቢያ መታወቂያውን አንዴ ከተቀበሉ ወደ “Status” ገጽ ይመለሱ እና የማመልከቻዎን ሁኔታ ያረጋግጡ።